# Learning by Ear 2013

"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" – "መዘዙን መቀበል"

EPISODE 23: ትንሽ ልትደሰች ይገባሻል

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: አልማዝ AND THE GIRLS ARRIVE IN TANDIKA**

- **ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **አልማዝ (F, 16)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ሊዲያ (F, 15)**
- **3 MORE GIRLS (15/16)**

**SCENE 2: በለጠ AND ዳንኤል WORKING OUTSIDE**

- **በለጠ (M, 16)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

**SCENE 3: ሉሊት AND THE GIRLS TALK BUSINESS**

- **ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **አልማዝ (F, 16)**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ሊዲያ (F, 15)**
- **3 MORE GIRLS (15/16)**

**<u>INTRO</u>**

## 1. NARRATOR:

**ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ "መዘዙን መቀበል"የተሰኘዉ ሁለተኛው ዙር ድራማ 23 ኛ ክፍል ነው። ይህን ክፍል ከማድመጣችን በፊት እስኪ እስከዛሬ የነበረዉን ታሪክ መለስ ብለን እናስታዉስ፤**

**ዳንኤል እና ምህረት በቦንጎ አካዳሚ ውስጥ የአንድ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከወራት በፊት ጥንቃቄ ሳያደርጉ ወሲብ ፈጽመው ምህረት አርግዛለች፡፡ አሁን የዳንኤል ሴት ጓደኛ አልማዝ ከሀገሩ ከላቦሪያ በልውውጥ መረሃ ግብር ተማሪነት ወደ ቦንጎ አካዳሚ ተዛዉራ መጥታለች፡፡ እርሷ እና ምህረትም ጓደኛ ሆነዋል።ዳንኤል ሁለቱንም ሴቶች ያጣ ይመስላል።**

## 2. EPISODE 22, LINES 117 – 120:

<u>ዳንኤል:</u> *(…)*አልማዝ፣ ወደ እኔ እንድትመለሺ እፈልጋለሁ

<u>አልማዝ</u>: ምን? እራስህን አልሳትክም አይደል ዳንኤል ?

<u>ዳንኤል</u>: አልማዝ ከምህረት ጋር ስለተፈጠረው ነገር አዝናለሁ፡፡ ተጸጽቻለሁ! ለእኔ ምኔም አይደለችም!

<u>አልማዝ</u>: ዳንኤል ስታሰጠላ!

## 3. NARRATOR:

በምህረት እናት ወ/ሮ ሉሊት አእምሮም ብዙ ነገር ይመላለሳል፡፡ ባለቤታቸው አቶ ሙላቱ በዘራፊነት ተጠርጥረው ለወራት ፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል፡፡ ወ/ሮ ሉሊት ከአንድ ዓመት በፊት የወለዷት ልጃቸውን ባለቤታቸው ለአካባቢው ፖለቲከኛ እንደሸጠባቸውም አውቀዋል፡፡ ህፃኗን ለማስመለስ ከ ረጅም ጊዜ አንስቶ በፖሊስ ጣቢያ በመመላለስ ላይ ናቸው።

***KW BEGIN***

## 4. EPISODE 22, LINES 16 – 17:

<u>ሉሊት</u>*:* ኦፊሰር ስለ ሂደት አትንገረኝ! (…) ማየት የምፈልገው ትንሿን ልጄን ነው!

<u>ፖሊስ ሙሉጌታ</u>: እመቤት፣ ባክሽን ድምጽሽን ቀንሺ፡፡ አዲሷ አለቃዬ ትሰማሻለች፡፡ እና እርግጠኛ ነኝ፤ ድምጽሽን በመስማትዋ አትደሰትም

***KW END***

## 5. NARRATOR:

ዛሬ

ዛሬ ለሉሊት የተሻለ ቀን ሊሆን ነው። እስቲ አሁን «ትንሽ ልትደሰች ይገባሻል» የተሰኘዉን ድራማ ዘና ብላችሁ ተከታተሉ

## <u>SCENE 1: አልማዝ AND THE GIRLS ARRIVE IN TANDIKA</u>

## 6. ATMO: TANDIKA SLUMS, INSIDE ምህረት'S HUT

## 7. GIRLS: HEARD CHATTING OUTSIDE (FROM INSIDE)

**8. SFX: KNOCK ON DOOR**

**9.** ሉሊት: ይግቡ ክፍት ነው!

**10. SFX: DOOR OPENS, FOOTSTEPS OF MANY PEOPLE**

**11.** ሉሊት: ውይሠላም፣ ልጆች! ሁላችሁም የመጣችሁት ምህረትን ለመጠየቅ ነው? እንኳን ደህና መጣችሁ! **(shouts to** ምህረት**)** ምህረት፣ ጓደኞችሽ መጥተዋል!

**12.** አልማዝ: እንደምን ዋሉ፣ የምህረት እናት፣ እኔ አልማዝ እባላለሁ፣ እሷ ትዕግስት፣ ያቺ ሊዲያ፣ ይችኛዋ ረድኤት፣ እሷ ደግሞ ህሊና፣ ይችኛዋ ሳራ ናቸው። ሁላችንም በአንድ የወጣት ማዕከል ውስጥ እንገናኛለን፡

**13. GIRLS:** እንደምን ዋሉ፣ የምህረት እናት…ሰላም ምህረት!

**14.** ምህረት: **(surprised)** እንዴት ዋላችሁ ! እንዴት ደስ ይላል! ምን ትሰራላችሁ እዚህ?

**15. GIRLS: HUGS AND HAND CLAPS AS THEY GREET EACH OTHER**

**16.** ሉሊት: **(to the girls):** ዋው፣ እንዲህ ብዙ የሚጠይቀን ሰዎች ካየን ረጅም ጊዜ ሆኖናል! እባካችሁ፣ ተቀመጡ! ቤቱ ትንሽ ቢሆንም፣ ግማሾቻችሁ አልጋው ላይ ሌሎቻችሁ ደግሞ ሳጥኖቹ ላይ ተቀመጡ…

**17. SFX: WATER CONTAINERS MOVED ON GROUND**

**18. SFX: CHAIRS CREAK**

**19. SFX: PEOPLE SITTING DOWN (CLOTHES RUSTLE)**

**20. SFX: BED CREAKING**

**21.** ምህረት: ልትጠይቁኝ በመምጣታችሁ ደስ ይላል!

**22.** አልማዝ: እውነቱን ለመናገር አንቺን ሳይሆን እናትሽን ለመጠየቅ ነው የመጣነው!

**23.** ምህረት/ሉሊት: ምን?

**24.** አልማዝ: የምህረት እናት፤ ይህ ጉብኝት ሌሎችንም ለማዳረስ በስፋት የያዝነው መርሃ ግብራችን አንዱ አካል ነው።

**25.** ምህረት: **(sudden realization)** ፣ እናንተ ግን ትገርማላችሁ! አትረቡም እሺ! ሁላችሁም! እንዴት እንደምትመጡ  አታሳውምነበር? በስፋት የተያዘውን መርሀ ግበር ያቀድነው አንድ ላይ ነበር!

**26.** አልማዝ: እንዴ ዋናውን ጉዳይ ከነገርንሽማ ምኑን ማስደነቅ ሆነ ታዲያ? እንደዛማ አይሆንም ምህረት!

**27. GIRLS:** **(chuckle)**

**28.** ሉሊት: እሺ ልጆች በሉ ንገሩኝ...ይህ ሌሎችን የማዳረስ ነገር፤ ቆይ ግንምን ላይ ነው የምትደርሱበት?

**29. GIRLS:** **(stifled laughter)**

***KW BEGIN***

**30.** ምህረት: **(embarrassed, whispers to** ሉሊት) እማዬ! እያሳፈርሽኝ ነው!

**31.** ሉሊት: **(loudly)** ተይ እንጂ የእኔ ልጄ መጠየቅ ስህተት ነው እንዴ?

**32.** አልማዝ: ኧረ አይደለም፤  የአቻ ለአቻ ማማከር አገልግሎት ለመስጠት ከመሰልጠኔ በፊት እኔም ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር።

**33.** ሉሊት: **(agrees*)*** ትክክል! መጠየቅ ጅልነት አይደለም፡፡ የማታውቂው እና ያልተረዳሽው ነገር ካለ መጠየቅ በምንም ተአምር ጅልነት አይሆንም?

***KW END***

**34.** አልማዝ: የምህረት እናት ይሄ በመስራታ ላይ ያለነው ህብረተሱቡን መድረስ ይባላል፡ ፡ በአካባቢ ያሉ ሰዎችን እየጎበኘን በሳምንቱ መጨረሻ አንዳንድ ነገር እናግዛቸዋለን፡፡

**35.** ሉሊት: ግን እዚህ ቤት ውስጥ ምን ማድረግ ትችላላችሁ? እኔ እዚህ ያለውን ነገር ሁሉ በሚገባ ይዤዋለሁ፡፡ ሲጀመር ቤቱም ትንሽ ነው፡፡

**36.** አልማዝ: ጠንክረው የሚሰሩ እናቶቻችንን ምን ያህል እንደምናደንቃቸው ማሳየት እንፈልጋለን፡፡ የምህረት እናት ዛሬ ቤት ውስጥ መንጎዳጎድ የሚባል ነገር የለም፡፡ ምግብ ማብሰሉን፣ እቃ ማጠቡን፣ ሌሎች ስራዎችን ሁሉእኛ እናከናውናለን፡፡ ትንሽ ረፍት እና ሳቅ ይገባዎታል፡

**37.** ሉሊት: ነው እንዴ! ...ያማ ጥሩ ደስ ይላል፡፡ ግን እኔ ምን እንዳደርግ ይጠበቅብኛል? ቀኑን ሙሉ የመቀመጥ ልማድ የለኝም፡

**38.** አልማዝ: ዛሬ ግን የሚያደርጉት ያንን ነው፡፡ ትዕግስት፣ የእናታችንን ታጣፊ መቀመጫ አዘጋጂ፡

**39.** ትዕግስት: እሺ፡

**40. SFX: FOLDING CHAIR UNFOLDED**

**41.** ሉሊት: ምንድን ነው እሱ?

**42.** አልማዝ: እናቶችን በምንጎበኝበት ወቅት እኛ ስራውን ስንሰራ እነሱ የሚቀመጡበትን ወንበር ይዘን እንሄዳለን። የእናታችን ታጣፊ መቀመጫ እንለዋለን እና የትዕግስት ኃላፊነት እናቶችን መንከባከብ ነው፣

**43. GIRLS LAUGH**

**44.** ትዕግስት: የምህረት እናት እኛ የሚያስፈልግዎትን ነገር ሁሉ ስንሰራ እርሶ ውጪ እዚህ ወንበር ላይ ዘና ይበሉ። እዛ ላይ ቁጭ ብለው የሚያስፈልጎት ነገር ሲኖር ጮክ ብለዉ ይጣሩ፣

**45.** ሉሊት: **(happily)** እሺ። ይሄማ ደስ እንደሚለኝ ተሰፋ አደርጋለሁ።። የተቀመጥኩበትን የመጨረሻ ጊዜ አላስታውሰውም፣

**46. SFX: FOOTSTEPS AS ትዕግስት AND ሉሊት GO OUT**

**47. GIRLS LAUGH**

***KW BEGIN***

**48.** አልማዝ: **(shouts after them)**ሌላው ነገር ፣ ምግብም አምጥተናል። ምን አበላቸዋለሁ ብለው አይጨነቁ።**(to the girls)** እሺ፣ ሴቶች በሉ አሁን እራሳችንን በቡድን እንከፋፍል። ሊዲያ፣ ሳራ እና ረድኤት ከትዕግስት ጋር ቡድን ሀ- ውስጥ ትሆናላችሁ። ምህረት፣ ሀሊና እና እኔ ቡድን ለ-ውስጥ። ቡድን ሀ-ዎች ከሰል ማንደጃውን ውጪ አውጡ። ዛሬ ምግብ የምናዘጋጀው ውጪ ይሆናል፣

**49.** ሊዲያ: ግን እኮ አልማዝ፣ ከሰል አቀጣጣዮች ከከባቢ አየር ጋር ወዳጅነት የላቸውም፣

**50.** አልማዝ: ጥሩ ነጥብ ነው ያነሳሽው፣ ሊዲያ። በሚቀጥለው ስብሰባችን የአካባቢ ብክለትን የማያስከትሉ የማብሰያ ዘዴዎችን እንዴት ማስተዋወቅ እንደምንችል እንነጋገርበታለን። ዛሬ ግን ማንደጃውን እንጠቀማለን። ቡድን ለ- ቤቱን ሙልጭ አድርገን እናጸዳለን። እሺ፣ አሁን ሁልሽም ወደ ስራሽ!

**51. SFX: UTENSILS UNPACKED, RUSTLING ETC.**

***KW END***

**52. MUSICAL INTERLUDE (HAPPY MUSIC)**

**<u>SCENE 2: በለጠ AND ዳንኤል ARE WORKING OUTSIDE</u>**

**53. ATMO: BONGO ACADEMY: EXTERIOR, WEEKEND, QUIET ENVIRONMENT**

**54. SFX: CLOTHES BEING WASHED IN BIG BASIN BY HAND**

**55.** በለጠ: **(to himself)** ኤጭ!አሁንስ ይሄ ልብስ አጠባ የሚባል ነገር ነው ያስጠላኝ። የሳምንት የእረፍት ቀኔን በአጠቃላይ እዚሁ አዳሪ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ይበላብኛል…

**56. SFX: STEPS ዳንኤል APPROACHING**

**57.** ዳንኤል: **(trying to be friendly)** ሄይ፣ በለጠ፣ አጠባው እንዴት ነው?

**58.** በለጠ: **(indifferent)** ሃይ ዳንኤል ጥሩ ነው፣ ይመስገነው።

**59.** ዳንኤል: ስማ በሳምንቱ መጨረሻ መስራት አይደላኝም! ገና የአትክልት ስፍራውንመኮትኮት አለብኝ…

**60. SFX: HOE AS SOMEONE DIGS WET EARTH**

**61.** ዳንኤል**:** ደደብነቴ ያመጣው ጣጣ ነው... **(laughs but** በለጠ **doesn’t. Pause)** እሺ፣ በስራ የተወጥረህ ትመስላለህ

**62.** በለጠ: **(still indifferent)** ልክ ነው። እኔው ካልሰራሁት ማን ሊሰራልኝ ነው ታዲያ?

**63.** ዳንኤል: ይህንን የምትሰራልህ የሆነች ሴት ማግኘት አትችልም?

**64.** በለጠ: **(not amused)** ምን? -ፕፍፍ...የተቀየርክ መስሎኝ ነበር!

**65.** ዳንኤል: **(ignores the comment)** ሄይ፣ ምናልባት በኋላ ላይ ቅርጫት ኳስ መጫወት እንችላለን?

***KW BEGIN***

**66.** በለጠ **(No response)**

**67.** ዳንኤል: ስማ፣ በለጠ፣ ከአንተ ጋር መዞር ነው የናፈቀኝ።

**68.** በለጠ: **(sarcastic)** ከምር?

**69.** ዳንኤል: **(sighs)** ደደብ እና አጉል ተመፃዳቂ እንደ ነበርኩ አውቃለሁ። ግን በጣም ይቅርታ! ባክህ አናግረን እንጂ! እዚህ ኪሲምባ ውስጥ ያለኝ ብቸኛ ጓደኛ አንተ ነህ...

***KW END***

**70.** በለጠ: ታውቃለህ ዳንኤል፣ ባህሪህን መቀየር ያለብህ ይመስለኛል። ማለቴ ሁሉም ነገር ዝም ብሎ በቀላሉ የሚገኝ አይምሰልህ።

**71.** ዳንኤል: ፣ በሌ ዋና ሰው፡፡ ምን ሆነሃል? ቀድሞ እኮ ይቅርታ ጠይቄሀለሁ! ሴታ ሴት ነገር ሆንክብኝ! ጓደኛዬ፣ አልማዝ ይህን ምናምን ነገር ሁሉ አእምሮህ ውስጥ ጠቀጠቀችብህ እንዴ?

**72.** በለጠ: **(annoyed)** *አየሀ* ምን ማለቴ እንደሆነ? አንተ ባክህ መቼም አትለወጥም፡፡ መቀጣተህ  እንኳን ምንም ለውጥ አላመጣም፡፡ አልማዝ የአንተ አይደለችም .

**73.** ዳንኤል: እኔ እንኳን ቢያንስ እንደ ወንድ ቅጣቴን እየፈፀምኩ ነው!

**74.** በለጠ: **(sarcastic)** በአበባው መስክ ውስጥ ልክ ነው! ታውቃለህ ዳንኤል? በቃ ተወኝ፡፡ እኔ እና አንተ ጓደኛ መሆን የምንችል አይመስለኝም፥ .

**75.** ዳንኤል**:** እሺ አሪፍ! የፈለገው ይሁን!

**76. SFX: FOOTSTEPS - ዳንኤል WALKS OFF ANGRILY**

**77. SFX: WASHING SOUNDS AS በለጠ CONTINUES WITH LAUNDRY**

**78. MUSICAL INTERLUDE**

## <u>SCENE 3: ሉሊት AND THE GIRLS TALK BUSINESS</u>

**79. ATMO: TANDIKA SLUM ATMO, OUTSIDE**

**80. SFX: CUTLERY ON PLATES AS THEY EAT**

**81.** ሉሊት: **(happily)** ምምም፡፡ እንዴት ይጣፍጣል ልጆች!  **(jokes)** ይህን የሰራው ማን ነው? እስዋን በልጄ ልለዋወጣት እችላለሁ? ምህረት ሄዳ ከእስዋ ወላጆች ጋር ስትኖር እሷ ደግሞ ከእኔ ጋር መቀመጥ ትችላለች፥

**82. GIRLS LAUGH**

***KW BEGIN***

**83.** ምህረት: **(jokes)** ልክ ነው! እናቶችንም መለዋወጡ ጥሩ ሀሳብ ሳይሆን አይቀርም፣ ምክንያቱም የእኔ እናት እንደሆነ ይኸው የእናትነት ታጣፊ ወንበሩ የተመቻት ይመስላል፡፡ ሁላችሁም ከሄዳችሁ በኋላማ የቤቱን ስራ ብቻዬን ሳልሰራው አልቀርም!

**84. GIRLS LAUGH**

***KW END***

**85.** ሉሊት: እናንተ ልጆች ስለመጣችሁ ደስ ብሎኛል፡፡ እንዲህ የሳቅኩበት ቀን ትዝ አይለኝም፡፡

**86.** አልማዝ: የምህረት እናት፣ እንድንመጣ ስለፈቀዱልን ተደስተናል፡፡ ግን እዚህ የመጣነው ምግብ አብስለን በልተን ደስ የሚል ጊዜ እንዲኖረን ብቻ አይደለም፡፡ ከእርስዎ ጋር የሆነ ነገር መነጋገርም እንፈልጋለን፡፡ .

**87.** ሉሊት: ምንድን ነዉ፣ አልማዝ?

**88.** አልማዝ: **(struggling)** ሀምም፣ እንዴት እንደምጀምረው አላዉቅም… በወጣት ማዕከሉ የቤተሰቦቻችንን የገንዘብ አቅም እንዴት እንደምናሻሽልም እንወያያለን፡፡

***KW BEGIN***

**89.** ሉሊት: **(upset)** ምን ማለትሽ ነው? ድሆች ነን እያልሽ ነው? ምህረት፣ ለጓደኞችሽ ምንድን ነው ስትነግሪያቸው የነበረው ?

**90.** ምህረት: **(embarrassed)** ምንም፣ እማዬ!

**91.** አልማዝ: እባክዎን፣ የምህረት እናት፣ ላናድድዎት ፈልጌ አይደለም። ግን እርስw ብቻዎን ምህረትን እና ወንድሞቿን መንከባከብ እንደማይቀልዎ እናውቃለን…

**92.** ሉሊት: **(cuts in)** እውነትሽን ነው፣ ቀላልማ አይደለም። ግን እየተወጣሁት እንደሆነ ይሰማኛል።

**93.** ምህረት: እንዴ! በደንብ እየተወጣሽውማ ነው እማ!

***KW END***

**94.** አልማዝ: ግን እስኪ የምህረት እናት  አስቡት፤ አነስ ያለች ንግድ ቢጤ  ቢኖርዎት…

**95.** ሉሊት: እሱማ ፣ በርግጥ ድንቅነገር  ነበር! ግን አይቻልም። ያንን ያህል እውቀት እንዳይኖረኝ ትምህርቴን ያቋረጥኩት ከመጀመሪ ነው፤

**96.** አልማዝ: ትምህርትዎን ስላላጠናቀቁ ምንም አያውቁም ማለት  አይደለም።

**97.** ምህረት: እማዬ፣ አልማዝ ልክ ናት! ብዙ ነገር ታውቂያለሽ! ለምሳሌ አያታችን ጓሮ ስለሚገኙት አትክልቶች ሁሉ በደንብ ታውቂያለሽ፤

***KW BEGIN***

**98.** ሉሊት: ያ እማ እውነት ነው… ቤተሰቦቼን እርሻቸው ውስጥ ማገዝ ሁሌም እወድድ ነበር። እናቴ አሁንም እዚያ ገጠር ብዙ አትክልቶችን  ታመርታለች…

**99.** ምህረት: **(cuts in)** ልክ ነው! ግን  ሁሉንም በልቶ የሚጨርሳቸዉ ስለሌለ አብዛኛውን ጊዜ መሬት ላይ ወድቀው በስብሰው ይቀራሉ!

**100.** ሉሊት: ልክ ነው… ያ ያሳፍራል…

**101.** አልማዝ: አዩ የምህረት እናት፣  ከገጠሩ አካባቢ ይልቅ እዚህ ከተማ ውስጥ ብዙ ሰዎች አትክልት ለመብላት ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ፤

**102.** ሉሊት: እውነት ነው…

**103.** ምህረት: ስለእዚህ እማዬ፣ ለምን የአትክልት ንግድ አትጀምሪም?

**104. GIRLS: (they all agree)**

**105.** ሉሊት: እናንተ ልጆች፣ አላውቅም። እንደዛ አይነት ስራ ለመጀመር ገንዘብ ከየት አገኛለሁ?

**106.** አልማዝ: በትንሹ ሊጀምሩ ይችላሉ እኮ!

**107.** ሉሊት: እንደዛ ስትይ ምን ማለትሽ ነው?

***KW END***

**108.** አልማዝ: ከገጠር አካባቢ አትክልቶች ቢያመጡ እና እዚህ ከተማ ውስጥ ቢሸጡስ? የሚያስፈልጎት ነገር አትክልቶቹን ወደዚህ ማጓጓዝ ብቻ ነው። በመጀመሪያ ገበያ ውስጥ መሸጥ ቢጀምሩ ቀስ በቀስ የራስዎት መደብር ይኖሮታል…

**109.** ምህረት: ጥሩ ሀሳብ ነው፣ እማዬ። በእርግጥ ለማጓጓዣ እንኳን ብዙ አናወጣም። እዛ ከገጠሩ አካባቢ ለጅምላ አከፋፋዮች የሚያቀርበው ሙሴ አለ። እዛ ወስዶ እቃውን ካከፋፈለ በኋላ ወደዚህ ሲመለስ መኪናው የሚመጣው ባዶውን ስለሆነ አትክልቶቹን ሊያመጣልን ይችላል።

**110.** ሉሊት: **(thoughtfully)** ሀምም! ያን ፈፅሞ አላሰብኩበትም ነበር። እዛ ትምህርት ቤታችሁ መጥቼ መማር አለብኝ።እናንተ ልጆች ሲበጣ ብልሆች ናችሁ!

**111. GIRLS LAUGH**

***KW BEGIN***

**112.** ሉሊት: አሁን ቅር የማይላችሁ ከሆነ ትንሽ ስጋ ቢዜ ለምጣ ፍቀዱልኝ፤ እጅ ያስቆረጥማል.

**113.** ትዕግስት: **(commanding)** የእናታችን ታጣፊ ወንበር ላይ አርፈው ቁጭ ይበሉ! እኔ እስከምፈቅድ ድረስ የትኛዋም እናት የመነሳት መብት የላትም! ባላያትም እንኳ ማለት ነው፤ **(to** ሊዲያ) ሊዲያ፣ ለምህረት እናት እስኪ ትንሽ ስጋ አምጪ!

**114.** ሊዲያ: **(jokes)** እሺ ጌታዬ! **(clears her throat)** …,ማለቴ እመቤቴ

**115. GIRLS (laugh)**

**116.** ሉሊት: **(shouts)** ባካችሁ ትንሽም ቢሆን ለልጆቼ ለቅዱስ እና ብሩክ አስቀሩላቸው። ከጨዋታ መልስ እቤት ሲደርሱ ሁሌም ተርበው ነዉ,,, እኔን እንዲውጡኝ አልፈልግም!

**117. GIRLS LAUGH**

***KW END***

**118. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

በስተመጨረሻ በአቶ ሙላቱ ቤት ሳቅ ተሰምቶአል። መቼም ከወጣት ማዕከሉ ለመጡት ለአልማዝ እና ሌሎች ሴቶች ልጆች ምስጋና ይግባቸው ማለት ነው ለሉሊት የታቀደው አዲስ ፕሮዤስ ከምን ይደርስ ይሆን? ትቀጥልበትስ ይሆን? በሌላ ጊዜ ቀጣዩን ክፍል ድራማ ይዘን እንመለሳለን። የዛሬዉን ድራማ በድጋሚ ማድመጥ ከፈለጉ በድረ-ገጽ አድራሻችን **dw.de/lbe** ላይ ያገኙታል። በእውኑ ዓለም ስለሚከሰቱ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ለማድመጥ ደግሞ የአማርኛውን ክፍል የሬዲዮ ዝግጅት ይከታተሉ። ድራማዉን ከድረገፅ አድራሻችን ላይ አውርደው በግል መዝገቦ ላይ መገልበጥይችላሉ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። ጤና ይስጥልን!